Turning Inspirations into Income

Email: contact@shegasab.com
Land line: +251 115 57 97 57
Mobile: +251 980 37 38 39

Shegasab

Shegasab Training and Consultancy PLC

## የገበያ እና ዳታ ክልከላ መብቶች (Data and Market Exclusivity rights) ምንድ ናቸው?

በፋርማሲቲካል ምርምር ዘርፍ አዲስ መድሃኒት ወደ ገበያ የማምጣት ሂደት (ክሊሊኒካል ሙከራዎች ጨምሮ) ከ10 አመት በላይ ሊወስድ እንደሚችል ይታወቃል። ፓተንት ደግሞ የሚመዘገበው የምርምሩ መጀመሪያ ላይ ነው። ጉዳዩ ያለው እዚህ ጋር ነው።

## እንዴት?

የመድሃኒቱ የምርምር እና በመድሃኒት እና ምግብ ቁጥጥር ባለስልጣን ምዝገባ ተደርጎ ወደ ገበያ ለመግባት ፍቃድ ለማግኘት የሚደረገው ሂደት እስከ 15 አመታት(ምሳሌ ነው) ሊወስድ ይችላል። ይህ ማለት ፓተንት ጊዜ የሚቆጥረው መጀመሪያ ምዝገባ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ስለሆነ መድሃኒቱ ገበያ ውስጥ ገብቶ በፓተንት ተጠብቆ የገበያ ብቸኝነት መብት(market monopoly right) የሚያገኘው እጅግ ያጠረ ጊዜ ይሆናል። እዚህ ጋር ባነሳሁት ምሳሌ 5 አመት ብቻ

የፋርማሲዩቲካል ካምፓኒዎች በቢሊዮን ዶላር አውጥተው የሚሰሯቸው ምርምሮች የፓተንት የጥበቃ ጊዜያቸው በዚህ መልኩ ሲያጥር ምን ሊፈጠር ይችላል?

መልሱ ምርምር አድርገው ለምርምር ያወጡትን ዋጋ መልሰው ትርፍ ለማግኘት የሚያደርጉትን ሂደት ያከብደዋል እናም ሁለት አማራጮች አላቸው አንደኛው መድሃኒቱን በተጋነነ ዋጋ መሸጥ ሊሆን ይችላል ሌላኛው አዳዲስ ምርምር ከማድረግ መቆጠብ እና ትርፋማነታቸው ላይ ማነጣጠር ነው።

## ይህ እንዳይሆን ምን መደረግ አለበት ?

በመግቢያየ የጠቀስኩት የዳታ እና ገበያ ክልከላ መብት የሚመጣው እዚህ ጋር ነው። ይህ መብት የጀነሪክ አምራቾች (Generic Manufacturers) ወደ ገበያ እንዳይገቡ ከፓተንት መብቱ ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ (Independet of the Patent Protection) የክሊኒካል ሙከራ መረጃ (Clinical trial data) መከልከል (Data Exclusivity Right) እና ሆን ተብሎ የገበያ ፍቃድ ለተወሰነ ጊዜ(ብዙ ጊዜ ለ5 አመት) በመከልከል (Market Exclusivity Right) መድሃኒቱን የፈጠረው ካምፓኒ የተራዘመ የገብያ ብቸኝነት መብት እንዲኖረው ማድረግ ነው።

ይህ መብት በመድሃኒት እና ምግብ ቁጥጥር ባለስልጣን የሚሰጥ ሲሆን የዳታ ክልከላ እና የገበያ ክልከላ መብቶችም ሁለት የተለያዩ መብቶች ሲሆኑ በጋራ ወይም በተናጠል ሊሰጡ ይችላሉ።

*ጥያቄ ካለዎት ወይም የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ በየሳምንቱ የነጻ ጥያቄ እና መለስ ፕሮግራማችንን ወይም በትሬኒንግ ውስጥ ከተዘረዘሩ ስልጠናዎች መካከል መርጠው ይመዝገቡ። ወይም ኮንታክትን በመንካት ያግኙን!*

© [2025] Shegasab. All Rights Reserved. The unauthorized reproduction, distribution, or transmission of this text is strictly prohibited and subject to legal action under applicable copyright law.